
# በፈረንሳይ አገር ውስጥ ስሥራ ያለኝ መብት መንድ ነው ?




## በምንም ሁኔታ ብትሆኑም በፈረንሳይ አገር ውስጥ መብት አላችሁ።

**በየወሩ** ደመውዝ ሊሰጣችሁ ይገባል።




**በሣምንት ከ6 ቀናት በላይ** መሥራት አትችሉም።





**በቀን ከ10 ሰዓት በላይ** መሥራት ይለባችሁም።



**በጽሑፍ የተቀመጠው የሥራ ውል መብታችሁ እንዲጠበቅላችሁ ይረዳችኋል።**


**ማስጠንቀቂያ፤ የሥራ ውል የሚገዛ ወይም የሚሸጥ ነገር አይደለም።**

ታክሶቹ ተቀንሰው በአንድ ሣምንት ውስጥ 35 የሥራ ሰዓታት ተሠርተው ወራዊ አነሥተኛው የደመውዝ መጠን ወደ **1443€* (ማለትም በሰዓት 12,02€ ነው)።**




* ይህ የ*2026* ነው። በየዓመቱ ይጨምራል። በ*2025 1426€* ያክል ነበር።


ለመኖሪያ ቦታችሁ* ካልሆነ በስተቀር አሠሪያችሁ ላገኛችሁ አገልግሎት ወይም ለተሠራ ስህተት ከደመውዛችሁ ገንዘብን መቀነስ አይችልም።



*ስለ ገንዘቡ መጠን እርግጠኛ ካልሆናችሁ የሥራ ተቆጣጣሪ ድርጅትን (አንስፔክስዮ ዲዩ ትራቫይ) አማክሩ።


**በሕጋዊ ሁኔታ ባትሆኑም**

- **በሆስፒታል ሕክምና ማግኘት**
- **ለፖሊስ አቤቱታ** ማቅረብ
- **የሥራ ተቆጣጣሪ ድርጅትን** ማግኘት **ትችላላችሁ።**




## ምክር

- **የማንነት ወረቀታችሁን እና ፎቶኮፒው** በእጃችሁ ላይ እንዲኖሩ አድርጉ።
- **በስማችሁ** የባንክ ሒሳብ ክፈቱ።




**የሰውን ምቾት የሚያሟላ የመሥራት እና የመኖር ሁኔታ** (ምግብ፥ መጣጠቢያ፥ ሙቅ ወኃ፥ የቤት ማሙቂያ ወዘተ.) እንደሚኖራችሁ አረጋግጡ።
**ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎችን** ለመጠየቅ ወደኋላ አትበሉ።
**መኖሪያ ቦታ** የተሰጣችሁ ከሆነ **በጥሩ ሁኔታ ሰው ሊኖርበት የሚችል መሆን አለበት።**




**እነዚህ መብቶቻችሁ እየተከበሩ አይደለም ? በሥራ ቦታችሁ ላይ የዛቻ ወይም የግፍ ችግር ተፈጥሮባችኋል ? አንዳንድ ነገር ለመሥራት ገድ እንደሆነባችሁ ይሰማችኋል ?**

**እርዳታ ጠይቁ !**

Depuis 1994
RENDRE VISIBLE L'INVISIBLE
COMITÉ CONTRE L'ESCLAVAGE MODERNE


169Bis Bld Vincent Auriol
75013 Paris

01.44.52.88.90

info@ccem.org

www.esclavagemoderne.org